# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## የ6ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና

## አማርኛ, 2015ዓ.ም/ 2023እኤአ

**የጥያቄ ብዛት**: 40 **የተፈቀደው ሰዐት**: - 1 ሰዐት

## አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመመረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡ መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት፡፡

ፈተናውን ሰረቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዐት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል፡፡

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት፡፡

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !**

መመሪያ 1- ከዚህ በታች ባለው ምንባብና ሰንጠረዥ መሰረት ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች ከተዘረዘሩላቸው አማራጮች መካካከል ይበልጥ መልስ ይሆናል የምትሉትን በመምረጥ በመልስ መስጫው ቦታ ላይ ጻፉ ፡፡

## ምንባብ

ደራሲና ገጣሚ በዕውቀቱ ሥዩም በጎጃም ክፍለሀገር ደብረማርቆስ አካባቢ የተወለደ ሲሆን በት/ቤት ውስጥ በሚኒሚዲያ በሚያቀርባቸው ሥራዎቹ የሥነጽሁፍ ተሰጥኦውን አዳብሯል፡፡ በ1995ዓ.ም ከአ/አበባ ዩኒቨርሲቲ በሳይኮሎጂ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል፡፡ ከስራዎቹ መካከል ቀጣዮቹ ይጠቀሳሉ፡፡

| ተ.ቁ | የመጽሐፍት ርዕስ | የድርሰት ዓይነት | የህትመት ዘመን |
|---|---|---|---|
| 1 | ኗሪ አልባ ጎጆዎች | የግጥም መድብል | 1995 |
| 2 | የ'ሳት ዳር ሃሳቦች | የግጥም መድብል | 2000 |
| 3 | ስብስብ ግጥሞች | የግጥም መድብል | 2001 |
| 4 | ድባብ | የግጥም መድብል | 2009 |
| 5 | አዳምዔል | የግጥም መድብል | 2012 |
| 6 | በራሪቅጠሎች | አጫጭር ልቦለዶች | 1996 |
| 7 | ወንዞች እስኪሞሉ | አጫጭር ልቦለዶች | 1998 |
| 8 | መግባትና መውጣት | አጫጭር ልቦለዶች | 2002 |
| 9 | እንቅልፍና እድሜ | ወጥ ልቦለድ | 1999 |
| 10 | ከአሜን ባሻገር | ታሪካዊ ወግ | 2008 |

በተጨማሪም በጋዜጦችና በተለያዩ መጽሔቶች ላይ‹‹ሶስተኛው ዓይን›› በተሰኘ አምዱ ላይ በሚጽፋቸው አዝናኝ ወጎቹ ይታወቃል፡፡ በአጫጭር ልቦለዶች ዘርፍ አገር-አቀፍ አሸናፊ በመሆን ተሸላሚና የሙሉ ጊዜ ፀሐፊ ነው፡፡

1. የደራሲው የመጀመሪያ ሥራ--------ይባላል፡፡
   ሀ. የማለዳ ድባብ ለ.ኗሪ አልባ ጎጆዎች
   ሐ.በራሪ ቅጠሎች መ.አዳምዔል
2. ሥለደራሲው ከተገለጹት መካከል <u>**የማይካተተው**</u> የትኛው ነው?
   ሀ.በሚኒሚዲያ በሚያቀርባቸው ሥራዎቹ ተሰጥኦውን አዳብሯል፡፡
   ለ.የሙሉ ጊዜ ፀሐፊ ነው፡፡
   ሐ.በሳይኮሎጂ ትምህርት ተመርቋል፡፡
   መ.ተሸልሞ አያውቅም፡፡

3. በሰንጠረዡ መሰረት ከደራሲው ሥራዎች ውስጥ አብዛኞቹ ከየትኛው የሥነጽሁፍ አይነት ይመደባሉ?

ሀ.ከግጥም ለ.ከአጭር ልቦለድ ሐ. ከረጅም ልቦለድ መ.ከወግ

4. ቀጥሎ ካሉት ሥራዎቹ መካከል ቀድሞ የታተመው----------ነው፡፡

ሀ- የማለዳድባብ ለ.ከአሜን ባሻገር ሐ.በራሪ ቅጠሎች መ.እንቅልፍና ዕድሜ

5. ደራሰው አገር-አቀፍ አሸናፊ የሆነው በየትኛው ዘርፍ ነው?

ሀ.በረጅም ልቦለድ ለ.በአጭር ልቦለድ ሐ.በግጥም መ. በወግ

***መመሪያ 2- ከተራ ቁጥር 6-10 ላሉት ጥያቄዎች ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል <u>በትርጉም የሚለየውን</u> ቃል የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።***

6. ሀ-ደንብ ለ-ሥርዓት ሐ-ህግ መ- ግብር

7. ሀ. በለሆሳስ ለ.በፍጥነት ሐ. በድምጽ አልባ መ. በዝምታ

8. ሀ. መላምት ለ. በግምት ሐ. በነሲብ መ. በዘዴ

9. ሀ. ስስታም ለ. ቸር ሐ. ንፉግ መ. ገብጋባ

10.ሀ-ተግዳሮት ለ. ችግር ሐ. ድፍረት መ. እንቅፋት

***መመሪያ 3- ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ልዩልዩ ጥያቄዎች መልስ ይሆናሉ ተብለው ከተቀመጡላቸው አማራጮች መካከል ይበልጥ መልስ የሚሆነውን በመምረጥ በመልስ መስጫው ቦታ ላይ ጻፉ ፡፡***

11.ሥለአንቀጽ ከተዘረዘሩት ውሥጥ **ሥህተት** የሆነው የቱ ነው?

ሀ- የሀሳብ ዝምድና ያላቸውን አረፍተ ነገሮች ይይዛል፡፡

ለ- ከአንድ በላይ ነጠላ ሀሳቦችን ይይዛል፡፡

ሐ- አነስተኛ የድርሰት ክፍል ነው፡፡

መ- አንድ ነጠላ ሀሳብ ብቻ ይይዛል፡፡

12.ቃላዊ ግጥም የማህበረሰቡ <u>አንጡራ ሀብት</u> ነው ፡፡ ለተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍችው----ነው፡፡

ሀ. ወርቅና ብር ለ-የሚሸጥ ሐ-የግል መ-ፈላጊ ያጣ

13. በትክክለኛው የሥዓተነጥብ የተፃፈው አ/ነገር የተፃፈው አ/ነገር የትኛው ነው?

ሀ. ለዚህ ደረጃ ላበቃችሁኝ ወላጆቼ፣ መምህሮቼ እና ት/ቤቴ እጅግ አመሰግናለሁ !

ለ. ለዚህ ደረጃ ላበቃችሁኝ ወላጆቼ፣መምህሮቼ፡፡እና ት/ቤቴ  እጅግ አመሰግናለሁ !

ሐ. ለዚህ ደረጃ ላበቃችሁኝ ወላጆቼ፣ መምህሮቼ፣ እና ት/ቤቴ እጅግ አመሰግናለሁ !

መ. ለዚህ ደረጃ ላበቃችሁኝ ወላጆቼ፡፡ መምህሮቼ፣ ት/ቤቴ እጅግ አመሰግናለሁ !

14.ትክክለኛውን አጻጻፍ የተከተለው የቀን አጻጻፍ የትኛው ነው ?

ሀ- ቀን 25/05/2015 ዓ.ም                ለ- ጥር 25/05/2015 ዓ.ም

ሐ- ጥር 25 ቀን /05/2015 ዓ.ም               መ- ቀን 25/05/2015 ዓ.ም

15.ቃላዊ ግጥምን የማይወክለው አገላለጽ የቱ ነው?

ሀ-የኑሮ ዘይቤንና ፍልስፍናን  ማሳያ ነው፡፡

ለ-በየአጋጣሚዎች ላይ የሚከወን የፈጠራ ድርሰት ነው፡፡

ሐ-የማህበረሰቡ ቅርስና ሀብት ነው፡፡

መ-የህይወትን መልኮች መግለጫ ኪነ-ጥበብ ነው፡፡

16.የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለው <u>መስተጋብር</u> ውስብስብ ነው፡፡  ለተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍችው-----ነው፡፡

ሀ-ትስስር        ለ-መደናገር        ሐ.ዝርያ        መ.ክፍል

17.አንቀጹ የሚያስተላልፈውን ሙሉ ሀሳብ የሚይዘው ዓረፍተ ነገር------ ይባላል፡፡

ሀ-ኃይለ ቃል        ለ- ዋና ዓረፍተ አገር

ሐ-መዘርዝር ዓረፍተ ነገር        መ -ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡

18.ሰዎች የምድርን አለም <u>በሚሰናበቱበት</u> ጊዜ  የሚከወን ነው፡፡ ለተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍችው----- ነው፡፡

ሀ-በሚያገቡበት        ለ-በሚሞቱበት     ሐ-በሚሰደዱበት    መ-በሚኮበልሉበት

*19.‹‹የጎበዝ ወዳጅ ታስታውቃለች፣*

*---------------- በለው ትላለች፡፡ ››*

ሀ- ከመሀል ገብታ    ለ- አፉፍ ቁጭ ብላ  ሐ- አፋፍ ላይ ቆማ  መ--እዳር ላይ ቆማ

20. ‹‹ **ወይም** ›› የሚለውን ቃል በመተካት የሚያገለግል ሥርዓተ ነጥብ-------ነው፡፡

ሀ  /        ለ  (  )        ሐ  ፤        መ  ‹‹ ››

21.ከዚህ <u>በኋላ</u> ግጥም መጻፍ እጀምራለሁ ፡፡ ለተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ፍችው----ነው::

ሀ. በፊት        ለ .ቀጥሎ        ሐ.መዳረሻ        መ.መጨረሻ

22. በትክክለኛው ሰዋስው የተጻፈው አ/ነገር የቱ ነው?

ሀ. በርካታ  ወንዞች ወራጆች  በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ፡፡  ለ. በኢትዮጵያ  ውስጥ በርካታ  ወራጅ ወንዞች አሉ፡፡

ሐ. በኢትዮጵያ በርካታ  ወንዞች ወራጅ ውስጥ አሉ፡፡        መ. በኢትዮጵያ ውስጥ  በርካታ  ወንዞች ወራጅ  አሉ፡፡

23.ከሚከተሉት አንዱ ከቃላዊ ግጥም **አይመደብም**፡፡

ሀ-እንጉርጉሮ ለ-ሆያ ሆዬ ሐ- ተረት መ . ቀረርቶ

24. ሰውዬው በየደረሰበት ፀብ ያለሽ በዳቦ ነው፡፡ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ.ነገር ፈላጊ ለ.ጋባዥ ሐ. አስታራቂ መ.ዳቦ ፈላጊ

25.‹‹ ያርሳል ያሳርሳል ያወጣል እዳሪ ፣

ሚስቱን አይላትም በቁጥብ እዳሪ ›› ይህ ቃላዊ ግጥም የ------- ግጥም ነው፡፡

ሀ. የሙሾ ለ. የልመና ሐ. የሥራ መ. የዘፈን

26.-ከሚከተሉት አንዱ ከጊዜ ተውሳከግስ **አይመደብም**፡፡

ሀ ክፉኛ ለ-ዛሬ ሐ- ቅድም መ-አሁን

27.እንግዳ ተቀባይነት <u>የኢትዮጵያዊነታችን</u> መገለጫ ነው፡፡ የተሰመረበት ቃል በምዕላድ ሲተነተን ትክክለኛው የቱ ነው?

ሀ. የ-ኢትዮጵያዊ-ነታችን ለ. የኢትዮጵያ-ዊ-ነታችን

ሐ. የ-ኢትዮጵያዊ-ነት-ችን መ. የ-ኢትዮጵያ-ዊ-ነት-አችን

28.‹‹ከአለባበስ ይቀደዳል ፣ ካነጋገር--------- ፡፡ ›› በሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ ባዶውን ቦታ የሚያሟላው ቃል ------ነው፡፡

ሀ.ያስታውቃል ለ.ይፈረዳል ሐ. ይሳሳታል መ. ይዋሻል

29. ሰዎች የምድርን አለም በሚሰናበቱበት ጊዜ በወዳጅ ዘመድ የሚዜም ቃልግጥም---------ይባላል፡፡

ሀ .የእንጉርጉሮ ለ.የሙሾ ሐ.የልመና መ.የልጅ ማባበያ

30. አስቴር በሁለተኛ ዲግሪ ተመረቀች ፡፡ በሚለው አ/ነገር ውስጥ የድርጊት ጊዜው -----ነው፡፡

ሀ.የአሁን ለ.የትንቢት ሐ-የወደፊት መ- የኃላፊ

31. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ቅድመ ግንድ ቅጥያ ያለው ቃል የትኛው ነው?

ሀ-ክንፋም ለ- ከተራራ ሐ-እውነት መ- ሠማይ

32. በትክክለኛው ሰዋስው የተጻፈው አ/ነገር የቱ ነው?

ሀ-በግጥም ውድድር ሞባይል አሸንፋ ተሸለመች፡፡

ለ- በሞባይል ውድድር አሸንፋ ግጥም ተሸለመች፡፡

ሐ-በግጥም ውድድር አሸንፋ ተሸለመች ሞባይል ፡፡

መ-በግጥም ውድድር አሸንፋ ሞባይል ተሸለመች፡፡

33.አንድ ቃል በቀጥታ ከሚኖረው ፍቺ ባሻገር የሚሰጠው ሚስጥራዊ ፍቺ --------ፍቺ ይባላል፡፡

ሀ-እማሬያዊ ለ-ፍካሬያዊ ሐ-ቀጥተኛ መ. መዝገበቃላዊ

34.ሥለ ተውላጠስም ሥህተት የሆነው-----ነው፡፡

ሀ- የግስ ክፍል ነው።

ለ-የስም ክፍል ነው።

ሐ-ነጠላና ብዙ ቁጠር አመልካች አለው ፡፡

መ- በአ/ነገር ውስጥ ስምን ተክቶ ያገለግላል፡፡

35. በመጥበቅና በመላላት ሲነገር ሁለት የተለያየ ትርጉም **የማይሰጠው** ቃል የቱ ነው?

ሀ.ሰባ ለ. ገና ሐ . ሥም መ. አያት

36. ዘምዘም <u>ቆቅ</u> ናት ፡፡ በሚለው አ/ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ፍካሬያዊ ፍችው----ነው፡፡

ሀ- ንቁ ለ- ወፍ ሐ- ፈሪ መ- በራሪ

37.ከሚከተሉት ቃላት መካከል ድህረ ግንድ ቅጥያ ያለው ቃል የትኛው ነው?

ሀ- አክስት ለ- ሥምንት ሐ- መጽሐፍሽ መ- ትምህርት ቤት

38. ---------ከት/ቤት ቅሪ ከሚሏት ሞቷን ትመርጣለች ፡፡ ለባዶ ቦታው ተስማሚው ተውላጠስም የቱ ነው ?

ሀ. እኔ ለ. እሱ ሐ. አንቺ መ. እሷ

39.ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የክርክር አቀራረብ መመሪያ <u>የሆነው</u>--------ነው፡፡

ሀ. ርዕስ መምረጥ ለ. አድማጮችን ማመስገን ሐ.መረጃ መሰብሰብ መ.ልምምድ ማድረግ

40.የሰለሞን እናት ቀይ መኪና አላቸው ፡፡ በሚለው አ/ነገር ውሥጥ ቅጽል የሆነው ቃል የቱ ነው?

ሀ.እናት ለ. መኪና ሐ.የሰለሞን መ.ቀይ